# ትንቢተ ሚክያስ (54)

## ጥናት አንድ ሚክያስ 1፡1-2፡13

የጥናት ዓላማ፡- በህይወታችን ወደፊት እንዳንሻገርና እግዚአብሄር ያዘጋጀልህን መልካም ነገር እንዳንወርስ መንገድህ መንገዳችንን በማጠር የከለከለንን ማናቸውንም ዓይነት ሁኔታ ሰብረን መሄድ እንድንችል ካስፈለገ፤ በህይወታችን የመሪነቱን ሥፍራ ሊይዝ እንደሚገባው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የሚሰብረው ወጥቶ በፊታቸው ይሄዳል፤ እነርሱም በሩን በመስበር ወጥተው ይሄዳሉ፤ እግዚአብሄር እየመራቸው ንጉሳቸው ቀድሚቸው ይሄዳል።" ሚክ 2፡13

1. ትንቢተ ሚክያስ 1፡1-2፡13 በአንድነት ይነበብ። ነብዩ ሚክያስ ቁ1-7 ላይ ስለ እግዚአብሄር አመጣጥ ሲናገር፤ እግዚአብሄር ከመኖሪያው ሥፍራ ወደ ምድር አመጣጡን ሲገልጽ ምን በማለት ነው የሚያስቀምጠው? ሚክያስ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ እግዚአብሄር አምላክ ይህንን ዓይነት አስደናቂና አስፈሪ በሆነ መንገድ ወደ ምድር እንደሚመጣ ሲተነብይ፤ የመምጣቱን ምክንያት ምን እንደሆነ ነው የሚናገረው?
2. በእስራኤል ዙሪያ የሚኖሩ ብዙ የአህዛብ ነገሥታት እንደ ሞዓባዊያን፣ ኤዶማውያን፣ አሞናውያን፣ ሶርያውያን፣ ፍልስጤማውያንና እነዚህን የከመሳሰሉት ሁሉ በእስራኤል ዙሪያ እንዳሉ እየታወቀና እስራኤልም ከእነዚህ ሁሉ የበለጠ ሐጥያት ስላደረጉ ነው ወይስ ለምንድነው እግዚአብሄር እንደዚህ በቁጣ በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ መውረድ ያስፈለገው? አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱሳችንን አካሄድና አስተሳሰብ ስንረዳ፤ እግዚአብሄር የዚህ ዓይነቱን መመሪያ ለመጠቀም የወሰነበት ምክንያት ሊሆን ይችላል የምትለውን ሃሳብ ተናገር።
3. በቁ8-9 ላይ ስናነብ ለእግዚአብሄር ሕዝብ እያስተላለፈ ያለውን ከባድ የሆነ ትንቢት አስመልክቶ ነብዩ በውስጡ እየተሰማው ያለውን ስሜቱን ሲገልጽ ይታያል፤ ነብዩ ዮናስ በዮና 3፡4 ላይ ባስተላለፈው የፍርድ መልዕክትና በዚህ ቦታ ነብዩ ሚክያስ ያስተላለፈበትን ስሜታቸውን ስትመለከት የሚታይህ ልዩነት ምንድነው? እነዚህን ሁለት የብሉይ ኪዳን ነብያት በማነጻጸር ከተመለከትን ዘንድ፤ ታዲያ ለእኛ በዚህ ዘመን የእግዚአብሄርን የወንጌል መልዕክት ይዘን ለምንመጣላቸው ሰዎች ከዚህ ምን ዓይነት ትምህርት ልንቀስም እንችላለን ትላለህ?
4. በሚክ 2፡1-2 ላይ ነብዩ ያተኮረባቸውና ድርጊታቸውን የሚያገልጥባቸው ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ ተናገር። ሃጥያት የተባለ ማናቸውም ዓይነት ሃጥያት በእግዚአብሄር ዘንድ አጸያፊና ፍርድን የሚያስከትል እንደሆነ የታወቀ ነው፤ ታዲያ በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ላይ የምንመለከታቸው ሰዎች ሃጥያታቸውን ከሌላ ሃጥያት የተለየ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?
5. ሁለት ጊዜ በቁ2 ላይ የተነገረ የሰዎቹን የልባቸውን ሁኔታ የሚናገርና የሚያደርጉትን እንዲያደርጉ የሚገፋቸውን ነገር በአንድ ቃል ግለጽ። ለእነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ክፋትን ለማድረግ እየፈለጉ ነገር ግን ሁኔታው ስለማይፈቅድላቸው ወይም ደግሞ አቅሙ ስለሌላቸው ብቻ ሃጥያትን ከማድረግ የሚታገዱ ሰዎች እንደሚኖሩ የታወቀ ነው፤ ከዚህ አንጻር በቁ1 ላይ የምንመለከታቸውን ሰዎች ሁኔታቸውን ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ? አንተስ ሃጥያትን ከመፈጸም የሚያግድህ ነገር የሁኔታው አለመፍቀድና የአቅም ማጣትህ ወይም ሥልጣን ያለመኖሩ ጉዳይ ነው ወይስ እግዚአብሄርን የመፍራትህ ውጤት ነው?
6. ቁ3-5ትን ስናነብ እነዚህ ሰዎች በልባቸው ውስጥ የነበረውን አንድ ተጨማሪ ሃጥያት እግዚአብሄር ሲያጋልጠው እናነባለን፤ የእነዚህ ሰዎች ሃጥያት እንደሆነ አድርጎ እግዚአብሄር በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የሚናገረውና ለሚመጣው ፍርድም እንደ ምክንያት ሆኖ የተነገረው አንድ ሃጥያት ምንድነው? በመዝ 105፡44 ላይ እንደምንመለከተው እግዚአብሄር የሌሎች የሆነውን ለሕዝቡ እንደሚሰጥ ይታወቃል፤ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ሊያደርግ ያሰበውና ቀድሞ ያደርግ ከነበረው ተቃራኒ ሆኖ የምታየው ነገር ምንድነው?
7. የእስራኤል ነብያት የእግዚአብሄርን ሕዝብና ራሳቸውንም ጭምር እያሳቱ እንደሆነ እንመለከታለን፤ እነዚህ ነብያት ህዝቡን እያሳቱ ያሉት በምን ዓይነት መንገድ እንደሆነ ከቁ6-11 ውስጥ የምታየውን ተናገር። እነዚህ ሐሰተኛ ነብያት በቁ6 ላይ የምናያቸውን እውነተኛ ነብያት እንዳይናገሩ ይከልክሉ እንጂ፤ በእነዚሁ ቁጥሮች ውስጥ የሚናገሩትን የሚወዱላቸው፣ ጨምረውም እንዲተነብዩላቸው የሚያበረታቷቸው አይነት ሰዎች እንዳሉ እናያለን፤ እነዚህ ሐሰተኛ ነብያትና ሕዝቡ የሚያበረታቷቸውና ደስ የሚሰኙባቸው ምን ዓይነት መልዕክተኞችን ነው? ይህ ዓይነቱ ክስተት በዘመናችን ይታይ እንደሆነና እንዳልሆነ ውይይት ይደረግበት።
8. በቁ13 ላይ "በፊታቸው"፣ "እየመራቸው"፣ "ቀድሚቸው" የሚሉትን አነጋገሮች ስትመለከት፤ ሕዝቡ በሩን በመስበር ለመሄድ እንዲችሉ በዚህ ክፍል መሰረት ወሳኝ ሆኖ የምትመለከተው ነገር ምንድነው? ወደፊት እንዳትሄድና እግዚአብሄር ከፊትህ ያዘጋጀልህን መልካም ነገር እንዳትወርስና መንገድህን ያጠረውን ሰብረህ ለመሄድ እንድትችል ካስፈለገ፤ በህይወትህ መንፈስ ቅዱስ መቅደምና የመጀመሪያውን ሥፍራ ሊይዝ ይገባል።

# <u>ጥናት ሁለት ሚክያስ 3፡1-12</u>

የጥናት ዓላማ፡- ክርስቶስ ኢየሱስ በክቡር ደሙ የዋጃቸውን ቅዱሳኑን እንድናገለግል በተለየየ መልኩ በሕዝቡ ላይ ሲሾመን፤ ምሳሌያችን የሆነውን የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ለሕዝቡ ራሳችንን መስዋዕት በማድረግ ለመስጠት እንጂ፤ ሕዝቡን ለእኛ ምግብ እንዲሆንልን ያለውን በማራቆት መሰዋት እንዲሆንልን እንዳልሆነ ለመገንዘብና ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "መልካሙን ጠላችሁ፤ ክፉውን ወደዳችሁ፤ የሕዝቤን ቁዳ ገፈፋችሁ፤ ሥጋውንም ከአጥንቶቻቸው ለያችሁ፤ የህዝቤን ሥጋ በላችሁ፤ ቁዳቸውን ገፈፋችሁ፤ ዓጥንቶቻቸውንም ሰባበራችሁ፤ በመጥበሻ እንደሚጠብስ፤ በድስት እንደሚቀቀል ሥጋ ቆራረጣችኋቸው።" ሚክ 3፡2-3

1. ትንቢተ ሚክያስ 3፡1-12 በአንድነት ይነበብ። በምዕራፍ አንድና ሁለት ውስጥ አጠቃላይ ሕዝቡን ሁሉ አስመልክቶ የተነገረ ትንቢት ሲሆን፤ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ በእስራኤል መሪዎች ላይ ያተኮረ ትንቢት ነው የምንመለከተው። በቁ1-2 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር የያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዢዎች እንደ አገር መሪነታቸው ማወቅ እንደነበረባቸው ይጠብቅባቸው የነበረው አንድ ነገር ምን እንደነበረ ነው የምናየው? እነዚህ የያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዢዎች ማወቅ የነበረባቸውን ነገር ያለማወቃቸው መገለጫ ሆነው በቁ2 ላይ የተጠቀሱት ሁለት ነገሮች ምንና ምን እንደሆኑ ተናገር።
2. በሰውም ሆነ በእግዚአብሄር ዘንድ አጸያፊና አስከፊ የሆነ ነገር እያደረጉ እንደሆነ በቁ1-3 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ የተመለከትናቸው እነዚሁ የያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዢዎች በመባል የታወቁት ሰዎች፤ በቁ4 ላይ ወርደን ስናይ ሲያደርጉት የምንመለከተው አንድ ጥሩ ሃይማኖተኛ የሚያስመስላቸው ነገር ሲያደርጉ ይታያል፤ ይህ የሚያደርጉት ድርጊት ምንድነው? ለዚህ ሃይማኖታዊ ድርጊታቸው እግዚአብሄር አምላክ ምላሹ ምን እንደሆነና ለምን የዚህን ዓይነት ምላሽ እንደመረጠ ተናገር።
3. ቁ5ትን ማንበብ ስንጀምር ደግሞ ስለ ያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዢዎች መናገሩን ያቆምና በነብያቱ ላይ ፊቱን ያዞራል። በዚህ ስፍራ ለምናያቸው ነብያት እግዚአብሄር የሰጣቸው ስምን ምን የሚል ነው? ነብያትቱ በእስራኤል ሕዝብ መሃል እያደረጉ ያሉትን አሳፋሪና አጸያፊ ድርጊት ሚክያስ ሲያጋልጣቸው እናያለን። እነዚህ ነብያት በሕዝቡ መሃከል ሆነው እናገለግላዋለን ብለው በሚናገሩት ምስኪን ህዝብ ላይ ያካሂዱት የነበረው ነገር ምን ነበረ? የዚህ ዓይነቱ ልምምድና ድርጊት በዘመናችን ምን ያህል በሥፋት ተሰራጭቷል ብለህ ታምናለህ? አስረዳ።
4. ቁ6 እና ቁ7 ላይ ደግሞ የምንመለከተው ነገር ምንም እንኳን እግዚአብሄር እስከዛሬ ድረስ የታገሳቸው ቢሆንም ከአሁን በኋላ እንደማይታገሳቸውና ሊወስድባቸው ያለውን እርምጃ ሲናገር ምን በማለት ነው የሚገልጸው? በቁ8 ላይ ደግሞ ሚክያስ ሌሎቹን ነብያት በመተው የራሱን አገልግሎት አስመልክቶ ይናገራል። በዚህ ቁጥር ላይ ስለ ነብዩ ሚክያስ ስለራሱ በሚናገረው እውነትና፤ ከላይ በተመለከትናቸው ሃሰተኛ ነብያት መካከል የሚታየውን ጉልህ የሆነ ልዩነት ለመናገር ሞክር።
5. ቁ9-10ን በተለይም ቁ9 ላይ ስንመለከት ደግሞ ነብያቱን ለጊዜው ተወት በማድረግ እንደገና ወደ ስለ ያዕቆብ ቤት መሪዎችና ወደ የእስራኤል ገዢዎች በመመለስ ነብዩ ስለእነዚህ ሰዎች ድርጊት ሶስት ዓይነት ነገሮችን ይናገራል፤ በዚህ ቁጥር ላይ ስለመሪዎቹና ገዢዎቹ ተዘርዝረው የምናያቸው ሶስቱ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
6. ቁ11ድንና ቁ12ትን በምናነብበት ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሄር ሕዝብ እንዲያገለግሉ የተቀመጡትን ሶስቱም የእስራኤል መሪዎች አገልግሎታቸው በምን ላይ እንደተመሰረተ ይናገራል፤ በዚህ ክፍል ላይ መሪዎቿ፣ ካህናቷና፣ ነብያቷ ሁላቸውም አገልግሎታቸውን ሲሰጡ ከሕዝቡ የሚጠብቁትን ነገር በአንድ ቃል ግለጽ ብትባል ምን ትላለህ? ለጽዮን መፍረስና በእግዚአብሄር ፍርድ ውስጥ መግባት ዋነኛ ምክንያት አድርጎ ነብዩ የሚናገረው ማንን ነው? የሕዝብ መሪዎች የሆኑ ሁሉ፤ ሕዝቡ ለሚያልፍባቸው መከራዎች ተጠያቂዎቹ መሪዎቹ ሆነው እንዳይገኙ ዘወትር ራሳቸውን መመርመር መልካም መሆኑን ሊያስታውሱ ያስፈልጋል።
7. ስለያዕቆብ መሪዎችና የእስራኤል ገዢዎች በቁ2-3 ላይ የተነገረው ነገር፤ መቼም እግዚአብሄር መሪዎቹ የሕዝቡን ስጋና አጥንቱን ሳይቀር እንደሚበሉ ሲናገር የአነጋገር ዘይቤ እንጂ ቃል በቃል የሚተረጎም ነገር እንደሆነ ይታወቃል፤ ታዲያ በዚህ ሥፍራ ላይ መሪዎቹን በዚህ ሁኔታ ሲገልጻቸው ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል? የእግዚአብሄርን ቅዱሳን ለማገልገል የተሰጠህን ሃላፊነት ለራስህ የመጠቀሚያ ምንጭ ለማድረግ የምከርከበት ጊዜ ይኖር ይሆን? እግዚአብሄር ሕዝቡን እንድናገለግል ሃላፊነት ሲሰጠን የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ለሕዝቡ ራሳችንን መስዋዕት በማድረግ ለመስጠት እንጂ፤ ሕዝቡን ለእኛ ምግብ እንዲሆንልን ለመሰዋት እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርብናል።

# ጥናት ሶስት ሚክያስ 4፡1-5፡15

የጥናት ዓላማ፡- በሰዎች ዓይን ተመልሶ ሊቆምና ውበት ሊኖረው አይችልም ተብሎ የተደመደመውና ተስፋ የተቆረጠበት ነገር፤ በእግዚአብሄር እጅ ውስጥ ሲገባ ግን አስቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ ይልቅ እጅግ ያማረና የተዋበ ሆኖ ሊሰራ እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ስለዚህ በእናንተ ምክንያት ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች፤ ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፤ የቤተ መቅደሱም ኮረብታ አረም የበቀለበት ጉብታ ይሆናል። ሚክ 3፡12 "በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ተራራ ከተራሮች ልቆ ይታያል፤ ከኮረብቶች በላይ ከፍ ይላል፤ ሕዝቦችም ወደ እርሱ ይጎርፋሉ።" ሚክ 4፡1

1. ትንቢተ ሚክያስ 4፡1-5፡15 በአንድነት ይነበብ። የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ተራራ ወይም የጽዮን ተራራ በመባል የሚታወቀው በቁ1 ላይ ስንመለከት ከሌሎች ኮረብቶችና ተራሮች ሁሉ ልቆና ከፍ ብሎ እንደሚታይ ይናገራል፤ ይህ ሁኔታ የሚሆንበትን ጊዜ ነብዩ መቼ ነው ይለናል? በዚህ ቁጥር ላይ የእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ተራራ "ከተራሮች ልቆ ይታያል፤ ከኮረብቶች በላይ ከፍ ይላል" በማለት መናገሩ፤ የጽዮን ተራራ አንድ ቀን ባልታወቀ መንገድ ቁመቱ ጨምሮ ከኤቨረስት ተራራ በልጦ ይገኛል ማለቱ ነው ወይስ ካልሆነ ጸሐፊው ምን ለማለት ፈልጎ ይመስልሃል?
2. በቁ2-5 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚገዛበት ዘመን የሚሆነውን ነገር በጥቂቱ ያሳየናል። በዚህን ጊዜ ነብዩ ሚክያስ ይሆናል በማለት ከሚናገራቸው ሃሳቦች መሃል ጥቂቶቹን በመዘርዘር ለመናገር ሞክር። "ሰይፋቸውን ማረሻ ጦራቸውንም ማጭድ ያደርጉታል።" በማለት ነብዩ ሲናገር፤ እውነትም ጌታ በሚመጣበት ሰዓት ሰይፍ ወደ ማረሻ ወይም ደግሞ ጦር ወደ ማጭድ ቀጥቅጠው ይቀይሩታል ማለት ነው ወይስ ይህ አነጋገሩ ሌላ የሚገልጸው እውነት አለ ትላለህ?
3. በቁ6-13 ውስጥ ስናነብ ነብዩ ሚክያስ በሁለት በተለያዩ ዘመናት ውስጥ ሊፈጸሙ ያላቸውን ሁለት ዓይነት ነገሮች ጨምቆ በአንድ ሥፍራ ላይ አስፍሯቸው ነው የምንመለከተው። እነዚህ ሁለቱ በዚህ ክፍል ውስጥ ሰፍረው የምናገኛቸው የተለያዩ ናቸው ያልናቸውን ዘመናት የትኞቹ እንደሆኑ ለማሳየት ሞክር። በቁ11-13 ውስጥ ስንመለከት በመጨረሻው ዘመን ቁ11ላይ የአህዛብ መንግሥታት በኢየሩሳሌም ላይ እንደሚሰባሰቡ ሲናገር፤ እግዚአብሄር ደግሞ በቁ12 ስለ ሁኔታው እርሱ ያለውን አመለካከት ሲናገር እናየዋለን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ስለመሰባሰባቸው የሚናገረው ነገር ምንድነው?
4. በሚክ 5፡1-2 ውስጥ ነብዩ እንደ ወትሮው ሁለት የተለያዩ ዘመናትን ማለትም የቅርብንና የሩቅን ጊዜያት በትንቢቱ ውስጥ በማካተት ሲናገር እንመለከታለን። በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ተጠቅሰው የምናገኛቸው ስንት ገዢዎችን ትመለከታለህ? በተለይም በቁ2 ላይ ስለተጠቀሰው ገዢ፤ ስለ ማንነቱ፣ ስለአመጣጡ ሁኔታና ሌሎችም የምትገነዘባቸውን ነገሮች ዘርዝር።
5. በቁ4-5 ውስጥ ስለዚህ የእስራኤል ገዢ በመባል በቁ2 ላይ ስለተነገረው ሰው በሌሎች ቁጥሮች ውስ ከተመለከትናቸው ነገሮች ባሻገር የምታያቸውን እውነታዎች በመዘርዘር ተናገር። ስለዚህ የእስራኤል ገዢ ሆኖ ስለሚመጣው ሰው እነዚህን ሁሉ የተለያዩ ባህርያትና እውነታዎችን ከተመለከትን ዘንድ፤ ይህ የእስራኤል ገዢ በመባል የተነገረለት ማን እንደሆነና ለምንስ ደግሞ ወደዚህ ዓይነት ድምዳሜ መድረስ እንደቻልክ ተጨማሪ ጥቅሶችን በመስጠት ለማስረዳት ሞክር።
6. በቁ5-9 ላይ ያዕቆብ በአሶራውያን ሰራዊት ምድራቸው ሲወረርና ምሽጎቻቸውን ሁሉ ጥሶ በሚገባበት በዚያን ወቅት፤ ያዕቆብን የሚታደግና የሚረዳ እንዳለው እንዳለ ይናገራል፤ ያዕቆብ በዚህን ጊዜ የተማመነው በማን ይመስልሃል? በቁ10-15 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ በሕዝቡ መሃል ሊያደርግ የተዘጋጀውን ነገር "በዚያን ጊዜ" በማለት በቁ10 ላይ ይጀምራል። በሕዝቡ መካከል እግዚአብሄር በዚያን ጊዜ ሊያደርግ የተዘጋጀው ነገር ምን እንደሆነ የትታያቸውን ነገሮች ዘርዝር።
7. ወደ ኋላ መለስ ብለን በሚክ 3፡12 ላይ ስለ እግዚአብሄር ተራራ የተነገረውንና፤ በሚክ 4፡1 ላይ ደግሞ ስለዚሁ ስለ እግዚአብሄር ተራራ የተነገረውን በማነጻጸር ስንመለከት፤ እግዚአብሄር ከፍርስራሽና፣ ተመልሶ ሊሰራ ይችላል ከማይባል ተስፋ የሌለው ከሚመስለው ነገር ምን ዓይነትን ነገር ሲያወጣ ነው የምንመለከተው? በሕይወትህ የፈራረሰና እንደገና ተመልሶ ሊሰራ ይችላል ብለህ ተስፋ የቆረጥክበት ነገር አለህ ወይ? እግዚአብሄር አምላክ ጨርሶ ከፈራረሰና ተመልሶ ሊሰራ እንደማይቻል ተስፋ ከተቆረጠበት ነገር ውስጥ፤ የተዋበና መልካምን ነገር ማውጣት እንደሚችል መዘንጋት አይኖርብንም።

# ጥናት አራት ሚክያስ 6፡1-16

የጥናት ዓላማ፡- እስራኤል ዳዊትን የመሰሉ የእግዚአብሄር ፍርሃት የሞላባቸው ሰዎች እያሉ ኦምሪንና አክአብን የመሰሉ ክፉ ሰዎች በምሳሌነት በመከተል አምላካቸውን እንዳስቆጡ ሁሉ፤ እኛም የሕይወታቸውን ምሳሌ ለመከተል የምንመለከታቸውና ባህርያቸውን ለመኮረጅ የምንሞክራቸው ሰዎች ማንነት ከእግዚአብሄር ጋራ ለሚኖረን ግንኙነት እጅግ ወሳኝነት እንደሚኖረው ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "የዖምሪን ስርዓት የአክአብን ቤት ልምድ ሁሉ የሙጥኝ ብለሃል፤ ትውፊታቸውንም ተከትለሃል፤ ስለዚህ አንተን ለውድመት፣ ሕዝብህን ለመዘባበቻ አሳልፌ እሰጣለሁ፤ አህዛብም ይሳለቁብሃል።" ሚክ 6፡16

1. ትንቢተ ሚክያስ 6፡1-16 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ሥፍራ ማለትም በቁ1-3 ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር ከሕዝቡ ጋራ ያለውን ክርክሩን እንዲሰሙለት በምስክርነት የሚጠራቸውን እንመለከታለን፤ እነዚህ ለምሥክርነት ሲጠሩ የምናገኛቸው እነማን ናቸው? በእነዚሁ ቁጥሮች ላይ ስናነብ እግዚአብሄር ልክ በዳኛ ፊት ቀርቦ ሕዝቡን እንደሚፋረድ ዓይነት ለሕዝቡ ጥያቄ ሲያቀርብላቸው ይታያል፤ ሕዝቡ በክፍሉ ውስጥ የተጠየቋቸው ሁለት ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው?
2. እግዚአብሄር ከሕዝቡ ምላሽን ሳይጠብቅ እርሱ ለሕዝቡ አደረግሁ የሚላቸውን በቁ4 ላይ ብቻ ሶስት ዋና ዋና ሃሳቦችን ይጠቅስላቸዋል፤ እነዚህ እግዚአብሄር አደረግሁላቸው በማለት ለሕዝቡ የሚቆጥራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? እንዳልነው እነዚህ እግዚአብሄር ካደረገላቸው ታላላቅና ዋነኛ ነገሮች ውስጥ እንደሆኑ እናውቃለን፤ የእነ ሙሴ፣ አሮንና፣ የማርያም ማለትም የሰዎቹ ለእነርሱ መሰጠት ልክ ከሌሎቹ ሁለቱ ጋራ እኩል ሆኖ መቅረቡን ስናይ፤ እግዚአብሄር ለእኛ የሚሰጠንን ሰዎች አስመልክቶ ምን መማር እንችላለን?
3. በቁ5 ላይ ሕዝቡን ከግብጽ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማግባት እየመራ ባለበት ወቅት እግዚአብሄር አምላካቸው በሕይወታቸው ካደረጋቸው ብዙ ድንቅ ነገሮች መካከል እንዲያስታውሱ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮችን እንመለከታለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በዚህ ቁጥር ላይ ስንመለከት፤ እነዚህን ሁለት ነገሮች ማስታወሳቸው ለእስራኤል ልጆች የሚያስገኝላቸው ወይም የሚጠቅማቸው ነገር ምን እንደሆነ ነው እግዚአብሄር የሚነግራቸው? አንተስ የእግዚአብሄርን ጻድቅነት ለማስታወስ ከዚህ ቀደም በሕይወትህ ያደረጋቸውን ድንቅ ነገሮች እንድታስታውስ ሊነገርህ ያስፈልግ ይሆን?
4. በቁ6-7 ላይ ስንመለከት እስራኤል የእግዚአብሄርን ክስ በመስማት ሃጥያተኛነቱን እንዳመነ የሚጠቁሙን ሃሳቦች የትኞቹ እንደሆኑ ተናገር። ምንም እንኳን ሃጥያተኛነቱን ተቀብሏል የሚያሰኘንን ሃሳቦች ብንመለከትም፤ ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ግን ግራ የገባው ይመስላል። እስራኤል ምን ማድረግ እንደሚኖርበት ግራ ቢጋባም እንኳን የጠየቃቸውን ሶስት ጥያቄዎች ስትመለከት በሶስቱም ላይ ለሃጥያቱ ስርየት እንደ መልስ አድርጎ የተቀበለው ማዕከላዊ ነገር ምንድነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ8 ላይ የተነገረውን ሃሳብ ስናነብ፤ እግዚአብሄር አምላክ ለሰው ልጆች፣ በተለይም ለእስራኤል ፈቃዱን ለማስታወቅ ይህ የመጀመሪያው ጊዜ እንዳልነበረ የሚያስረዳን የትኛው ሃሳብ ነው? እነዚህ ሁሉ በቁ7 ላይ የተጠየቁትን ጥያቄዎች ስንመለከት፤ ጥያቄዎቹ መቅረብ የነበረባቸውና ለሕዝቡ ጥያቄዎች ደግሞ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት መቻል የነበረበት ማን እንደ ነበረና በምንስ ምክንያት ሕዝቡ ወደዚህ ግራ ወደ ተጋባበት ሁኔታ እንደደረሰ ተናገር።
6. ካህናቱ ሕዝቡን ለመርዳት ፈቃደኞች ባይሆኑና ገንዘብን የሚያሯሩጡ ቢሆኑ እንኳን፤ እግዚአብሄር ግን ለእነርሱ አሳልፎ ሳይሰጣቸው ለጥያቄአቸው መልስ ሲሰጣቸው ይታያል። እጥርና ምጥን ባለ መልኩ እግዚአብሄር ከእነርሱ የሚጠብቃቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። ሰዎቹ በቁ7 ላይ መልስ ለማግኘት የጠየቋቸውን ጥያቄዎች አዎችን የሚል ምላሽ ቢሰጣቸው ለማድረግ የተዘጋጁ ከሆነ፤ በቁ8 ላይ እግዚአብሄር ከጠየቀው ነገር ጋራ ሲተያይ የትኛው እንደሚከብድ ተናገር።
7. በሃጥያቱ ምክንያት እግዚአብሄር አምላክ በእስራኤል ላይ ሊሆንበት ያለውን ነገሮች በቁ14-15 ውስጥ በዝርዝር ሲነግረው እንመለከታለህ፤ እነዚህ በእስራኤል ሃጥያት ምክንያት በምድሪቱ ላይ ሊያመጣቸው እንዳለ የተነገሩት ክፉ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
8. በቁ16 ላይ እስራኤል የዳዊትንና የመሳሰሉትን የእግዚአብሄር ፍርሃት ያደረባቸውን ሰዎች ምሳሌ ከመከተል ይልቅ በክፋታቸው የታወቁትን ኦምሪንና አክአብ የተባሉት አባትና ልጅ ክፉ ባህርይ ምሳሌ አድርገው እንደተከተሉ ይነግረናል። በ1ኛ ነገ 16፡25-33 ላይስለ ኦምሪና ስለ አክአብ ባህርይ ምን እንመለከታለን? አንተስ ምሳሌ አድርገህ የምትከተላቸው ሰዎች እግዚአብሄርን የሚፈሩ ናቸው ወይስ እግዚአብሄርን የሚያሳዝኑ? በምሳሌነት የምናያቸውና ባህሪያቸውን ለመኮረጅ የምንሞክራቸው ሰዎች እግዚአብሄርን የሚፈሩ ዓይነት ሰዎች ሊሆኑ ያስፈልጋል።

# <u>ጥናት አምስት ሚክያስ 7፡1-20</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የገባውን ቃል ኪዳን ጠባቂ አምላክ መሆኑ ለክርስትና ሕይወታችንና ለእምነታችን መሰረታዊ የሆነ ነገር መሆን ብቻ ሳይሆን፤ በእርሱ ላይ እምነታችንንም ለማድረግ የሚያስችለን ዋነኛ ባህርዩ እንደሆነ ለማስታወስና ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ፤ ለአባቶቻችን በመሃላ ቃል እንደገባህላቸው፤ ለያዕቆብ ታማኝነትን፤ ለአብርሃምም ምህረትን ታደርጋለህ።" ሚክያስ 7፡20

1. ትንቢተ ሚክያስ 7፡1-20 በአንድነት ይነበብ። እህል በሚሰበሰብበት ወቅት ለድሆችና ለመበለቶች እንዲሁም ለመጻተኞች ምግብ እንዲሆን እግዚአብሄር ለእስራኤል ሥርዓትን የደነገገ ሲሆን ነብዩ የሚበላ አንዳች ነገር እንደሌለ ይናገራል። ቁ2ትን ስናነብ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነውን ሲናገር ለምንድነው ይለናል ይህ ዓይነቱ ክፉ ነገር በምድሪቱ ላይ የመጣው? ከቁ1-3 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ ስንመለከት ሕዝብን እንዲያገለግሉ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በትክክለኛው መንገድ እንዳልተጠቀሙበት የሚያሳየን ሃሳብ የትኛው እንደሆነ ተናገር።
2. በቁ3 ላይ ያለው "ሁሉም አንድ ላይ ያሴራሉ።" የሚለው ሃሳብ እነዚህ በየግላቸው እጅ መንሻን የሚቀበሉት፣ ፍርድ ለመስጠት በዳኝነት ተቀምጠው በጉቦ የሚፈርዱትና በሃይላቸው ደግሞ የፈለጉትን የሚያስፈጽሙት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ማሴራቸው አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው ብለህ ታምናለህ? በቁ4 ላይ የምናነበው "ይሻላል የተባለው ሰው" እና "እጅግ ቀና የተባለው ሰው" ምን እንደሚመስል ስትመለከት፤ በምድሪቱ ላይ ስላለው ሁኔታና ስለ ሰው ባህርይ ምን ዓይነት ግምጋሜ ላይ ያደርሰናል ትላለህ?
3. በህዝቡ መካከል የሚታየው ሃጥያት በተለያዩ አቅጣጫዎች ብዙ ነገሮችን እንዳበላሸ ቢታወቅም እንኳን፤ በቁ5 ላይ ግን አንድ ጉልህ ሆኖና ተገልጦ የምንመለከተውን በሕብረተሰቡ መካከል ያበላሸው ትልቅ ነገር ምንድነው ትላለህ?
4. በዚህ በቁ7 ላይ ስንመለከት ሰውየው ራሱ እግዚአብሄርን ተስፋ ለማድረግና አምላኩን ለመጠበቅ እንደወሰነ "እኔ ግን" በማለት ተናግሯል፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ "አንተ ግን" በማለት ከሌሎች በተለየ አካሄድ እንዲሄድ የተነገረው ሰው ማን እንደሆነ ተናገር። ከቁ1-6 ውስጥ ያለውን ሁኔታ ተመልክቶ በቁ7ት ላይ "እኔ ግን እግዚአብሄርን ተስፋ አደርጋለሁ፤ አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠብቃለሁ" የሚለው የዚህ ሰው አመለካከት እንባቆም በምዕራፍ3 ውስጥ ከደረሰበት ድምዳሜ ጋራ የሚስማማው በምን መንገድ ነው? አካባቢህ ሁሉ በከፋት መንገድ መበልጠግና ማደግ ሲሞክር አንተስ "እኔ ግን እግዚአብሄርን ተስፋ አደርጋለሁ" ብለህ ተስፋህን በአምላክህ ላይ ታጸናለህ ወይ?
5. ቁ9 ላይ በሃጥያት ምክንያት የደረሰባትን የእግዚአብሄር ቁጣ በመቀበል ፍጻሜው ወደ ብርሃን መውጣትና ጽድቁን ማየት እንደሆነ እናነባለን፤ ይህንን ክፍል በዕብራዊያን 12፡10-11 በማነጻጸር ስትመለከት በሁለቱ ጥቅሶች መሃል ማየት የሚቻለው የሃሳብ ተመሳሳይነት ምንድነው ትላለህ? በቁ8 እና በቁ10 ላይ በእስራኤል ውድቀት ደስ የሚሰኝና እግዚአብሄር እግዚአብሄር የምትለው ነገር ሁሉ ከንቱ እንደሆነ የሚናገር ጠላት እንዳለ የሚታይ ሲሆን፤ እስራኤል ግን በዚህ ክፍል ውስጥ ስለወደፊቱ ቢያንስ ስለ ሁለት ነገሮች እርግጠኛ ሆኖ እንመለከተዋለን፤ እነዚህ ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
6. ከቁ8-10 ድረስ እስራኤል የእግዚአብሄርን ቅጣት ከተቀበለች በኋላ እግዚአብሄር እንደሚያስባትና ጠላቶቿ ደግሞ እንደሚያፍሩ ሲናገር፤ በቁ11-12 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር ራሱ ስለሕዝቡ የሚያየውን ሲናገር ነው የምናነበው። እግዚአብሄር በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ለሕዝቡ እያየለት ያለው ነገር ምንድነው? በቁ15-17 ውስጥም በተጨማሪ እግዚአብሄር አምላክ ለሕዝቡ ወደፊት ሊያደርግ ያለውን ነገሮች ሲናገር እናያለን፤ እነዚህ ተጨማሪ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር።
7. በቁ18-19 ውስጥ ጸሐፊው አጉልቶ የሚያሳየን የእግዚአብሄር ባህርይ ምንድነው?
8. ቁ18-19 ካየነው የእግዚአብሄር ባህርይ በተጨማሪ ቁ20 ላይ ደግሞ ከእግዚአብሄር ባሕርያት መሃል በሌላኛው ላይ ትኩረት አድርጎ ሲናገር እናያለን፤ ይህ በዚህ ሥፍራ ተተኩሮበት የምናገኘው የአምላክ ባህርይ ምንድነው? ይህ የእግዚአብሄር ባህርይ በአንተ ህይወት ውስጥስ ምን ያህል ተገልጦ አይተኸው ታውቃለህ? እግዚአብሄር የገባውን የቃል ኪዳን የሚጠብቅ አምላክ መሆኑ ለክርስትና ሕይወታችንና ለእምነታችን መሰረታዊ የሆነ ነገር መሆኑን ሁልጊዜ ልናስታውስ ያስፈልገናል።